የሰ/መ/ቁ 40804

ጥር 26 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ዳንዲቦሩ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ - ጠበቃ እስክንድር ዘውዴ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪዎች፡-**1/ ተክሉ ኡርጋ ኢደኤ - ቀረቡ፡፡

2/ ቶሎሳ መገርሳ ባልቻ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የአሠሪና ሠራተኛ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሾች የነበሩት የአሁኖች ተጠሪዎች ናቸው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረቱት የስራ ውላችን ከህግ ውጭ አቋርጦብናል በማለት ነው ፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ የሥራ ውሉ የተቋረጠው የትምህርት ሚኒስቴር ባወጣው መመሪያ መሠረት ተማሪዎችን ተቀብሎ ማስተማር ባለመቻሉ ነው በመሆኑም ከሕግ ውጪ የተፈፀመ ነገር የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ እንደ ክርክሩ ያስረዳል ያለውን ማስረጃ አያይዞ ስለማቅረቡ ክሱን ባስተናገደው ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ ተገልጾአል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክርም ከሰማ በኂላ የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ በማለት ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ ከዚህ ውሳኔ በመነሳትም አመልካች የስራ ውል ከሕግ ውጪ ሲቋረጥ ሊከፍሉ የሚገባቸውን ክፍያዎች ለተጠሪዎች ይከፈል ብሎአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ውድቅ አድርጐአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች መስከረም 15 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የስራ ውሉ ከሕግ ውጪ ነው የተቋረጠው በሚል የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው ተጠሪዎች በአመልካች ኮሌጅ በመምህርነት ተቀጥረው ሲሠሩ የነበረ ሲሆን፣ አመልካች የስራ ውሉን ያቋረጠው ተቀጥረው ሲሰሩበት የነበረው የስራ ክፍል በበቂ ምክንያት ተሰርዞአል፡፡ ሥራው የለም በማለት ነው ፡፡ተጠሪዎችም ክሱን የመሠረቱት ሥራው ስላለ ወደ ስራችን እንመለስ በማለት ሳይሆን ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነውና ልዩ ልዩ ክፍያዎች ይከፈሉን በማለት ነው፡፡ በአሠሪና ሠራተኞች ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 28(1)(መ) እንደተመለከተው ሠራተኛው ጉዳይ የያዘው የስራ መደብ በበቂ ምክንያት ሲቀርብና ሠራተኛውን ወደ ስራ ቦታ ማዛወር የማይቻል ሆኖ ሲገኝ የሥራ ውሉ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ማቋረጥ ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪዎች ይሠሩበት የነበረው የሥራ መደብ /የማስተማር ስራ/ መንግስት ባወጣው መመሪያ መሠረት መሠረዙን በማስመልከት አመልካች ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪዎችም ይሄንኑ አልካዱም መንግስት ያወጣው መመሪያ ከመስከረም ወር 2000 ዓ.ም ጀምሮ ከግል ትምህርት ተቋሞች የሚመረቁ ዕጩ መምህራን በመንግስት

የትምህርት ተቋ

ሞች እንደማይቀጠሩ መታዘዙን የሚያመለክት ነው፡፡ ተጠሪዎች ተቀጥረው ይሠሩ የነበሩትም እጩ መምራንን ማሰልጠን ነው፡፡ መመሪያው ከወጣ በኋላ ግን ለመሠልጠን ተማሪ ሊመዘገብ አልቻለም፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ተጠሪዎች ይሠሩበት የነበረው የሥራ መደብ የለም ማለት ነው፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች እንደመልሱ ያስረዳልኛል ያለውን ማስረጃ ከመልስ ማመልከቻው ጋር አያይዞን እንዳቀረበለት በውሳኔው ላይ ገልጿል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መዝገቡ ለቃል ክርክር በተቀጠረበት ዕለት ነገረ ፈጁ አልቀረበም፤ የሚል ምክንያት በመስጠትና ማስረጃ እንደሌለው በመግለጽ አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ ቀደል ሲል እንደተመለከተው አመልካች በዋነኛነት የጠቀሰው ማስረጃ የመንግስት መመሪያ ነው፡፡ በመንግስት የሚወጡ ሕጐች እና መመሪያዎች፣ ደንቦች፣ ወዘተ በግልጽ የሚታወቁ እንደመሆናቸው ፍ/ቤቶች (ዳኞች) ግንዛቤ የሚወሰዱባቸው ናቸው፡፡ ተከራካሪ ወገን ለክርክሩ የሚጠቅመውን ሕግ ከአስረጅነት አላቀረበም በሚል ክርክሩን በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ደግሞ አመልካች ለሥራ ውሉ ማስረጃ ስለማቅረቡ ፍ/ቤቱ በሚገባ መዝግቦለታል፡፡ ጉዳዩ ለቃል ክርክር በተቀጠረበት ዕለት ነገረ ፈጁ ባለመቅረቡ ማስረጃው እንደሌለ ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም፡፡ ሲጠቃለል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 30239 ግንቦት 18 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 68312 ሐምሌ 21 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ ሕግ ቁ 348 (1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል የነበረው የስራ ውል የተቋረጠው በሕጋዊ መንገድ ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

   መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ት